መልእክት አሥራ-አንድ

## ቦዔዝና ሩት ክርስቶስን እና ቤተ ክርስቲያንን በምሳሌ ማሳየታቸው

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፡- ሩት 1፡16-17፤ 2፡1-3፣ 13-16፤
3፡9፣ 12፣ 15፤ 4፡1-17፣ 21-22

**I. ከኢያሱ እስከ ሩት ባለው የእስራኤል ታሪክ ክፍል መጀመሪያና መጨረሻ የክርስቶስ ምሳሌ የሆኑ ሁለት ጎልተው የሚታዩ ሰዎች አሉ፤ የአንድን ማንነት ሁለት ገጽታዎችን የሚያመለክቱት እነዚህ ሰዎች ኢያሱና ቦዔዝ ናቸው—ኢያ. 1፡1፤ ሩት 4፡21-22፡-**

ሀ. በመጀመሪያ ኢያሱ በእግዚአብሔር የተመረጡትን ሕዝብ እግዚአብሔር ወደ ወሰነው በረከት ውስጥ በማምጣት ክርስቶስን በምሳሌ ያሳያል፤ በኢያሱ እንደተመሰለው፣ ክርስቶስ ወደ መልካሚቱ ምድር አምጥቶናል፣ ለእኛ ምድሩን የራሱ አድርጓል እና ለድሰታችን እንደ ርስታችን ምድሪቱን አከፋፍሎናል፤ ክርስቶስ ለእኛ መልካሚቱን ምድር አግኝቷል፣ በመጨረሻም እንድንደሰተው እርሱ ለእኛ መልካሚቱ ምድር ነው።

ለ. በመጨረሻ ቦዔዝ ለእርካታችን እንደሆነ ባላችን ክርስቶስን በምሳሌ ያሳያል።

**II. በሩት መጽሐፍ ቦዔዝ በሚከተሉት ገጽታዎች ክርስቶስን በምሳሌ ያሳያል፡-**

ሀ. በሀብት ባለጠጋ እና በመስጠት ለጋስ (2፡1፣ 14-16፤ 3፡15) እንደሆነው ሰው ቦዔዝ መለኮታዊ ብልጥግናዎቹ ፍለጋ የሌላቸው እና በተትረፈረፈ አቅርቦቱ የተቸገሩትን የእግዚአብሔር ሕዝብ የሚንከባከበውን (ኤፌ. 3፡8፤ ሉቃስ 10፡33-35፤ ፊልጵ. 1፡19) ክርስቶስ በምሳሌ ያሳያል።

ለ. ተፈላጊዎቹን ወራሾች ለማፍራት የመሐሎንን ርስት እንደ ተቤዠውና የመሐሎንን መበለት ሩትን ሚስቱ አድርጎ እንደ ወሰደው ዘመድ (ሩት 2፡3፤ 3፡9፣ 12) ቦዔዝ ለመጨመሩ ቤተ ክርስቲያንን የተቤዠውንና ቤተ ክርስቲያንን አቻው ያደረገውን ክርስቶስ በምሳሌ ያሳያል (ኤፌ. 5፡23-32፤ ዮሐ. 3፡29-30)።

ሐ. በመጽሐፈ ሩት መሠረት ቦዔዝ ሩትን ተቤዣት፣ ብኵርናዋንም ተቤዠ፤ ስለዚህ የክርስቶስ የሚታወቅ የቀደመ አባት ሆነ—4፡1-17፣ 21-22፤ ማቴ. 1፡5-6፡-

1. እንደ ወንድምና እንደ ቦዔዝ ስለራሳችሁ ብኵርና ብቻ ሳይሆን ሌሎች በክርስቶስ ስላላቸው ብኵርና ግድ መሰኘት አለባችሁ፤ በሌላ አነጋገር ስለራሳችሁ የክርስቶስ ድሰታ ብቻ ሳይሆን ስለ ሌሎችም የክርስቶስ ድሰታ ግድ መሰኘት አለባችሁ—ኤፌ. 3፡2፤ 1 ጴጥ. 4፡10-11፤ ማቴ. 24፡45-47።
2. በቤተ ክርስቲያን ያሉ ውዶች የብኵርና ድሰታቸውን፣ የክርስቶስ ድሰታቸውን በማጣት እንደ ሩት ሆኑ እንበል፤ እነዚህን ወድ ቅዱሳን ወደ ክርስቶስ ድሰታቸው መልሶ ለማምጣት በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ብዙ ቦኤዞች ሊኖሩን ያስፈልጋል።
3. መጽሐፈ ሩት ከቦዔዝ ይልቅ ለሩት ቅርብ የሆነ ዘመድ እንደ ነበር ይነግረናል፣ ያ ሰው ግን ራስ ወዳድ ነበር፤ ስለራሱ ብኵርና ብቻ ግድ ተሰኘ፡-
   ሀ. አንዳንድ ወንድሞች በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ያሉ ድሃ "ሩቶች" የሆኑትን መንከባከብ አለባቸው፣ ነገር ግን በክርስቶስ መንፈሳዊ ድሰታ ራስ ወዳድ ናቸው—ሕዝ. 34፡2-23።
   ለ. እውነተኛ ቦዔዝ የሆነና የክርስቶስ የበለጠገ ድሰታ ያለው ሰው እንዲህ ያሉትን ቅዱሳን ሙሉ ወደ ሆነ የክርስቶስ ድሰታ ለማምጣት ዋጋ ይከፍላል፤ ሌሎችን በዚህ መንገድ በእረኝነት በመንከባከብ፣ የበለጠ የክርስቶስ ድሰታ፣ ታላቁ የክርስቶስ ድሰታ ይኖረዋል፤ እለት በእለት ስለ ሌሎች የክርስቶስ ድሰታ ግድ መሰኘት አለብን—ምሳ. 11፡25፤ ሐዋ. 20፡35፤ 1 ጴጥ. 5፡1-4።

መ. እንደ ቦዔዝ የሚሆኑት እነርሱ በቤተ ክርስቲያን ሕይወት አእማድ ይሆናሉ (በመቅደሱ ውስጥ ካሉት አእማድ አንዱ ስሙ "ቦዔዝ" ተብሎ ተጠርቷል—1 ነገ. 7፡21 ኢ.መ.ት.)፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አምድ የአካሉን ሕይወት በተግባር በመለማመድ ውስጥ ያለ በመለወጥ የሆነ የእግዚአብሔር ግንባታ ምልክት፣ ምስክር ነው—ዘፍ. 28፡22፤ 1 ነገ. 7፡15-22፤ ገላ. 2፡9፤ 1 ጢሞ. 3፡15፤ ራእ. 3፡12፤ ሮሜ 12፡2፤ ኤፌ. 4፡11-12፡-

1. በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ አእማድ የሆኑ ሰዎች ለመሞትና ለመቀበር እንጂ ለምንም የማይገቡ በሥጋ ያሉ ሰዎች መሆናቸውን በመገንዘብ ያለማቋረጥ በእግዚአብሔር ፍርድ (ናስ) ሥር ያሉ ናቸው—መዝ. 51፡5፤ ዘጸ. 4፡1-9፤ ሮሜ 7፡18፤ ማቴ. 3፡16-17፡-
   ሀ. ምንም እንደሆንን እና ለመሰቀል ብቻ ብቁ እንደሆንን ራሳችን ላይ መፍረድ አለብን፤ የሆንነውን ሁሉ የሆንነው በእግዚአብሔር ጸጋ ነው፣ የምንደክም እኛ አይደለንም የእግዚአብሔር ጸጋ እንጂ—1 ቆሮ. 15፡10፤ ገላ. 2፡20፤ 1 ጴጥ. 5፡5-7።
   ለ. በአማኞች መካከል ላለው ክፍፍልና ፍሬ አልባነት ምክንያቱ ናስ ስለሌለ፣ የእግዚአብሔር ፍርድ ስለሌለ ነው፤ በዚያ ፈንታ ትዕቢት፣ በራስ-መመካት፣ እኔ ልክ ነኝ ማለት፣ ራስን-ማጽደቅ፣ ራስን-ትክክለኛ ማድረግ፣

ለራስ-ምክንያት መስጠት፣ የራስ-ጽድቅ፣ ሌሎችን መኮነን እና ሌሎችን በእረኝነት በመንከባከብና በመፈለግ ፈንታ ሌሎችን መቆጣጠር አለ—ማቴ. 16፡24፤ ሉቃ. 9፡54-55።

ሐ. ጌታን ስንወደውና እንደ ናሱ ሰው ስንለማመደው (ሕዝ. 40፡3) ልዩ የሆነ ፍቅራችን፣ ገደብ-የለሽ ገርነታችን፣ ወደር የሌለው ታማኝነታችን፣ ፍጹም ትህትናችን፣ የላቀ ንጽህናችን፣ ክፍ ያለ ጽድቃችንና ቅድስናችን፣ ብሩህነታችን እና ቅንነታችን ይሆንልናል—ፊልጵ. 4፡5-8።

2. በመቅደሱ አእማድ ላይ ባሉት ጉልላቶች ላይ እንደ መርበብ ሥራ ነበረባቸው፤ እነዚህ በእግዚአብሔር ግንባታ ውስጥ ያሉ አእማድ የሆኑ ሰዎች የሚኖሩበትና ኃላፊነት የሚሸከሙበት ሁኔታዎች የተወሳሰቡና የተደበላለቁ መሆኑን ያሳያሉ—1 ነገ. 7፡17፤ 2 ቆሮ. 1፡12፤ 4፡7-8።

3. በጉልላቶቹ ላይ ሊሊ አበባዎችና እና ሮማኖች ነበሩ—1 ነገ. 7፡18-20፡-

ሀ. ሊሊ እኛ በሆነው ነገር ሳይሆን በእግዚአብሔር ላይ ባለ እምነት የሆነ ሕይወትን፣ እግዚአብሔር ለእኛ በሆነው ነገር የመኖር ሕይወትን ያመለክታል፤ ናሱ ማለት "እኔ አይደለሁም" ሲሆን ሊሊ ማለት "ነገር ግን ክርስቶስ" ማለት ነው—መኃ. 2፡1-2፤ ማቴ. 6፡28፣ 30፤ 2 ቆሮ. 5፡4፤ ገላ. 2፡20።

ለ. የጉልላቶቹ ጉንጉን ላይ ያለው ሮማን እንደ ሕይወት የክርስቶስን ብልጥግናዎች ሙላት፣ መትረፍረፍና ውበት እና መገለጥ ያመለክታሉ—ፊልጵ. 1፡19-21፤ ኤፌ. 1፡22-23፤ 3፡19።

ሐ. በመረቡ የማስወገድ ሥራ እና በመርበቡ የመገደብ ሥራ በኩል በሕይወት ለሆነው የእግዚአብሔር ግንባታ የክርስቶስን መለኮታዊ ሕይወት ብልጥግናዎች ለመግለጥ በእግዚአብሔር የመታመን ንጹሕ፣ ቀላል የሆነን ሕይወት መኖር እንችላለን።

## III. በዚህ ብሩህና መዓዛ የተሞላ ታሪክ፣ ሩት በሚከተሉት መንገዶች ቤተ ክርስቲያንን በምሳሌ ታሳያለች፡-

ሀ. ሩት በእግዚአብሔር ፍጥረት በአዳም ውስጥ ያለች ሴት እና በሰው ውድቀት ሞዓባዊት (ኃጢአተኛ) መሆኗ፣ ከዚህም የተነሣ በእነዚህ ሁለት ገጽታዎች አሮጌው ሰው መሆኗ በምሳሌ የሚያሳየው ቤተ ክርስቲያን፣ ከመዳኗ በፊት፣ በእግዚአብሔር ፍጥረት ውስጥ እንዳሉ ሰዎች እና በሰው ውድቀት እንደ ኃጢአተኞች "አሮጌ ሰዋችን" እንደሆነች ነው—ሮሜ. 6፡6።

ለ. ሩት ያጣችውን የሞተ ባሏን ንብረት ሙብት ለመመለስ የሞተ ባሏን ዕዳ ያስወገደው ቦዔዝ የተቤዣት (ሩት 4፡9-10) የሞተ ባል መበለት መሆኗ በምሳሌ የሚያሳየው ያጣችውን በእግዚአብሔር የተፈጠረው የወደቀው የተፈጥሯዊውን ሰው ሙብት ለመመለስ (ዘፍ. 1፡26፤ ኢሳ. 54፡5) የአሮጌውን ሰዋን ኃጢአት ባስወገደው (ዮሐ. 1፡29) ክርስቶስ የተዋጀችውን ቤተ ክርስቲያንን የተሰቀለው ባሏ ከሆነው አሮጌው ሰዋ ጋር (ሮሜ 7፡4፤ 6፡6) ነው።

ሐ. ሩት ቦዔዝ ከተቤዣት በኋላ ለእርሱ አዲስ ሚስት መሆኗ (ሩት 4፡13) በምሳሌ የሚያሳየው ቤተ ክርስቲያን ከመዳን በኋላ የቤተ ክርስቲያን ተፈጥሮአዊ ሰው ዳግም በመወለዱ በኩል (ዮሐ. 3፡6) የክርስቶስ አምሳያ መሆኗን (ቁ. 29፤ ሮሜ 7፡4) ነው።

መ. ሩት ኑኃሚንን ወደ እስራኤል ምድር ለመከተል መምረጧ (ሩት 1፡16-17) እና ከቦዔዝ ጋር መጣመሯ በምሳሌ የሚያሳየው አሕዛብ ኃጢአተኞች የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል ርስት ይካፈሉ ዘንድ (ኤፌ. 3፡6) ከክርስቶስ ጋር መጣበቃቸውን(2 ቆሮ. 1፡21) ነው።

## IV. የቦዔዝ (ክርስቶስን እንደ አዲሱ ባላችን በምሳሌ በማሳየት) እና የሩት (ቤተ ክርስቲያንን የተሰቀለው ባሏ ከሆነው ከአሮጌው ሰዋ ጋር በምሳሌ በማሳየት) ስእል በጳውሎስ በ ሮሜ 7፡1-6 ተነግሯል፡-

ሀ. በእግዚአብሔር ፍጥረት ውስጥ የሰው የመጀመሪያው ስፍራ የሚስትነት ነበር፤ ኢሳይያስ 54፡4 ፈጣሪያችን ባላችን እንደሆነ ይናገራል፤ እንደ እግዚአብሔር ሚስት በእርሱ ላይ መደገፍና እርሱን እንደ ራሳችን መውሰድ አለብን።

ለ. ሰው ሲወድቅ ሌላ ስፍራ፣ የአሮጌው ሰውን (በእግዚአብሔር የተፈጠረው ነገር ግን በኃጢአት የወደቀው የራሳችን ማንነት) በራስ የተወሰነ ስፍራ ወሰደ፤ በእግዚአብሔር የተፈጠረው ሰው ሚስት ነበር፣ የወደቀው ሰው ግን ከእግዚአብሔር ኢ-ጥገኛ ሆነ፣ እንደ ባልም ራሱን ራስ አደረገ።

ሐ. አሮጌ ባል የነበረው አሮጌው ሰዋችን ከክርስቶስ ጋር ስለተሰቀለ (ሮሜ 6፡6)፣ ከሕጉ ነጻ ሆነናል (7፡2-4)፣ ለዘላለም ሕያው ሆኖ ከሚኖረው ማንነት ከአዲሱ ባላችን ከክርስቶስ ጋር ተጋጥመናል።

መ. እንደ አማኞች ሁለት ሁኔታዎች ወይም ስፍራዎች አሉን፡-

1. እንደ ወደቀው አሮጌው ሰው በእግዚአብሔር ላይ ጥገኛ የመሆንን የመጀመሪያውን የሚስትነት ስፍራ የተወው እና ከእግዚአብሔር በኢ-ጥገኛነት ለራሱ የባል እና ራስ የመሆንን ስፍራ የወሰደው አሮጌው ስፍራችን አለ።

2. ዳግም እንደ ተወለደው አዲስ ሰው፣ ለእግዚአብሔር እንደ እውነተኛ ሚስት (ኢሳ. 54፡5፤ 2ቆሮ. 11፡3)፣ በእርሱ ላይ ጥገኛ በመሆን እና እርሱን እንደ ራስ በመውሰድ ወደ መጀመሪያው እና ተገቢ ወደ ሆነው ስፍራ የተመለሰ አዲስ ስፍራ አለን።

ሠ. ስለተሰቀልን (ገላ. 2፡20፣ ሮሜ. 6፡6) አሮጌ የሆነው የባል ስፍራ የለንም፤ አሁን ያለን ክርስቶስን እንደ ባላችን የምንወስድበት እና (ከእንግዲህ ወዲህ አሮጌውን ሰው እንደ ባላችን ባለመውሰድ) በአሮጌው ሰው መሠረት ከቶ የማንኖርበት አዲሱ ስፍራ ብቻ ነው።

ረ. በሮሜ 7፡4 ላይ ጳውሎስ የቀብር ስነ-ሥርዓትን እና ሰርግን ጋር በአንድ ላይ ያስቀምጣል፤ በአንድ በኩል፣ ተቀብረናል፤ በሌላ በኩል ደግሞ አግብተናል፤ በአዲሱ ስፍራችን መሠረት ሌላኛውን እንድናገባ በአሮጌው ስፍራችን መሠረት ሙት ተደርገናል፤ በአዲሱ ስፍራችን መሠረት፣ ለእግዚአብሔር ፍሬን እንድናፈራ ከሙታን የተነሣውን እርሱን አግብተነዋል።

ሰ. “ለእግዚአብሔር ፍሬ እንድናፈራ፥ እናንተ ለሌላው፥ ከሙታን ለተነሣው፥ ለእርሱ ትሆኑ ዘንድ” (ቁ. 4) አሮጌው ሰዎችን፣ የቀድሞው ባላችን ከከርስቶስ ጋር ተሰቅሎአል፤ ይህ መጋጠም የሚስት በሆነው በአዲሱ ስፍራችን፣ በትንሣኤው ከክርስቶስ ጋር በማንነት፣ በስም፣ በሕይወት እና በሕልውና ሕይወታዊ ጥምረት እንዳለን ያሳያል።

ሸ. ዳግም እንደተወለደው አዲሱ ሰው እና እንደ ክርስቶስ ሚስት፣ የሆንነው እና የምናደርገው ሁሉ አሁን ከእግዚአብሔር ጋር የተገናኘ ነው፣ እግዚአብሔርም እንደ ሕይወታችን ፍሬ፣ ሞልቶ መፍሰስ ከእኛ ይወጣል፤ ይህ ከዚህ ቀደም አሮጌው ሰው፣ አሮጌው ባል ከሆነው ከእኛ ከሚወጣው ከሞት ፍሬ (ቁ. 5) በተጻራሪ ነው።

ቀ. አሁን እኛ በመንፈሳችን ካለው ሕይወት የሚሰጥ መንፈስ ከሆነው ከሞት-ከተነሣው ክርስቶስ ጋር ተጋጥመናል፤ ይህ የ“መንፈስ......ከመንፈሳችን ጋር” (8፡6) እንደ “አንድ መንፈስ” (1 ቆሮ. 6፡17) መጋጠም ነው፡-

1. መላው ማንነታችንን ወደዚህ የተጋጠመ መንፈስ ማዞርና መትከል አለብን—ሮሜ 8፡6።
2. በተጨማሪም በዚህ በተጋጠመው መንፈስ መሠረት መኖርና መመላለስ አለብን—ቁ. 4።
3. ስለዚህም በዚህ የተጋጠመ መንፈስ ስንኖር ለሦስታንዱ አምላክ ክብር የክርስቶስ ብዞዎች የተካተቱበት መገለጥ ለመሆን የክርስቶስን አካል መኖር እንችላለን—ኤፌ. 1፡23፤ 3፡21፤ 1 ቆሮ. 10፡31፤ 1 ጴጥ. 4፡11፤ ራእ. 21፡10-11።

© 2021 Living Stream Ministry